✝ይድረስ ለልዑል እግዚአብሔር!!!✝

ይድረስ በመላዉ ዓለም ተሰዶ ለሚንከራተተዉና ለሚሠቃየዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ!

✝ሁሉን ማድረግ በሚችለዉ አምላክበ ልዑል እግዚአብሔር ስም በረከቱ፣ ረድኤቱና

ሰላሙ ይድረሳችሁ አሜን!!! ✝

ዉድ የሀገራችን ልጆች፤ በኢትዮጵያዊነታችሁ ለምታምኑ ሁሉ በያላችሁበት ይህች አነስተኛ የእንባ ጽሁፍ ትድረስልኝ።

አእምሮ ካበጀሁበት ጊዜ አንሥቶ በዉድ ሀገራችን ላይ ብዙ ነገሮችን ሲፈጸሙ አይቻለሁ። ቀጥሎ የምጽፈዉ ለተነሣሁበት ዓላማ ጥቆማ እንጂ በሀገሪቱ ላይ የተፈጸመባትንና እየተፈጸመ ያለዉን ምናልባት ካሉ ለታሪክ ጸሀፊዎች እተዋለሁ። በንጉሡ ዘመን የጀመረን ግፍ እነሆ የሀገሪቱ መሬት የመንግሥት ይባላል። ከዚያም በጣሊያን ጦርነት ሕዝባቸዉን በትነዉ የሸሹት ንጉሥ የኢትዮጵያን አርበኞች መከራቸዉን አይተዉ ጠላትን ድል ሲነሡ ሕዝቡን እንደገና ወደጦርነት ለመመለስ ከኋላ የእንግሊዝን ጦር አስከትለዉ ሲመጡ አፈ ጮሌዎችና ባንዳዎች፤ የኢትዮጵያን አርበኞች ያስፈጁ የጣሊያን እንቁላል ጠባሾች ተቀበሏቸዉ። ከዚያም እንደገና ጦርነት ለመጀመር ከሞከሩ በኋላ የሕዝባቸዉ ሥቃይና ስደት ያሳዘናቸዉ ጀግኖች አባቶቻችን መከረዉ ጌታ ባወቀ ፍርዱን ይስጥ የወገናችን ሥቃይ ይብቃ ብለዉ ንጉሡን ይቀበላሉ። ተከትሎ የመጣዉ የእንግሊዝ ጦርም ተመለሰ።

የተቀበላቸዉ ባንዳና አፈጮሌ አርበኛ እየተባለ የመንግሥት የተባለዉን መሬት ታደለ። እዉነተኞቹም ምን ያድርጉ እነሱም እየተቀበሉ በየክፍላተ ሀገሩ ገብተዉ እርሻቸዉን ይዘዉ አገር ማልማታቸዉን ቀጠሉ። ከዚያ ንጉሡን በዉዳሴ ከንቱ የሚያሞጋግሱና የእነዚያ ባንዳዎች እርስት ጠባቂዎች በያሉበት ባላባት፣ ጭቃሹም እየተባሉ እየተሾሙ መሬት የለሽ አራሹን ወገን ማሠቃየት ማስጨነቅ መሠረቱን ጣለ። ይህ ግፍ ቀስ በቀስ በመላዉ የሀገሪቱ ሕዝብ ላይ ጥላዉን ጣለ። ጭራሹኑ ጀግኖች አባቶቹ በደማቸዉ ባስከበሯት ሀገር ሕዝቡን ጭሰኛ እያሉ መሬታቸዉን እያሳረሱ ጤፉን ጭነህ አምጣ ይሉ ጀመር። ከገጠር ወደከተማ ጤፉን ጭኖ የመጣ ገበሬ ምሳ የሚሰጠዉ የዘንጋዳ እንጀራ፤ እንዲያረባላቸዉ የተሰጠዉን ሙክት ጭኖ ሲመጣ የሚሰጠዉ ጎመን ነበር።

እንደዉ ባጭሩ ግፉ በዛ፤ ፍርድ ተጓደለ፤ ደሀዉ ተበደለ። ከጥቂቶቹ ንጉሣዉያንና ሹማንቶቻቸዉ በቀር ሁሉ ጭሰኛ ሆነ ጾም እና ሰንበት ተሻረ፤ በየሀገሩ ጠንቋይና አስማተኛ ሟርተኛ ባለዛር መተተኛ መሾም ሆነ። በቤተ መንግሥቱም መተተኛና ጋኔን ሳቢ አስገቡበት። ሕዝባቸዉንም እግዚአብሔርንም ረሱት። በቤተክርስቲያን በማያገባቸዉ ገብተዉ ያለ ሀገሪቱ ሥርዓት ካቴድራል ብለዉ ሾሙ። ሀገሪቱን ሃይማኖት የግል ሀገር የጋራ ብለዉ ሀገሪቱንና ሕዝቡን ከእግዚአብሔር አለያዩ። ከዚያ በኋላ ሥር የሰደደ የጠንቋይና የሟርተኛ ነገር ቀጥሎ ሁሉም ነገር በቡሽፍቱ በቆሪጥ ላይ ተጣለ። ቅንድቡ የገጠመ እየተባለ በባላገሩ ሕዝብ እየተሰማ ቅንድባችን የገጠመ ልጆች ከመንገድ ዳር አትቁሙ እየተባልን ነበር። ይህም በዛሬዉ አእምሮዬ ስገነዘበዉ ቡሾፍቱ ላይ ሰዉ እስከመሠዋት ደርሰዉ ነበር። በዚህ አላበቃም የንጉሡ ግፍ እጃቸዉን ወደቤተክህነቱ ዘረጉ። ሌላዉን ትቼ ጻድቅ ለመባል የተመቻቸላቸዉን መነኩሴ መርጦ ፓትሬያርክ ሾሙልን ተባለ። የመጀመሪያዉን ፓትሪያርክ እግዚአብሔር አልመረጠም፤ ሕዝብም አልመረጠም። ቤተክርስቲያን ያልመረጠቻቸዉን ፀሐዩ ንጉሥ ሾሙልህ ተብሎ በዉዳሴ ከንቱ ታጅቦ የመጣዉ ሁሉ የግፍ ጽዋ የሚቀዳለት ቅዱሱና የዋሁ ሕዝብ ጌታ ሾመልህ ተብሎ ሲነገረዉ እልል ብሎ ተቀበለ።

የተሾሙላት ቤተመንግሥት የቤተመንግሥቱን ሹማምንት ሲጸልዩለት ንጉሣዉያኑን በዉዳሴ ከንቱ ሲያሸቃብጡለት እየገቡ እየበሉ እየጠጡ ፀሐዩ ንጉሥ ሲሉ በሕዝቡ ላይ በአርሶ አደሩ ላይ የሚደርሰዉን ግፍ ሳይናገሩ ጠንቋይና ሟርተኛ ጋኔን ሳቢና ባለዛሩ ሁሉ ሲሾም ጾም ሲሻር መኳንንቱና መሳፍንቱ በየቤተክርስቲያኑ ያለሥጋወዱ ተክሊል እየፈጸሙ በእግዚአብሔር ቤት ሲዘብቱ አራት አምስት ሴት በየመሬታቸዉ ሲያስቀምጡ የጋብቻዉ ሥራዓት ሁሉ ሲፈርስ በደሀዉ ግፍ ሲሠራበትና ፍርድ ሲጓደል ጉቦ ሲነግሥ የንጹሓን ደም ሲፈስ ለቆሪጥ ሰዉ ሲገበር በሬዲዮ ሰዉ ጠፋ አፋልጉኝ ሲባል (ዛሬም በወያኔ በየቤተክርስቲያኑ አጥር የከተማዉ መኪና፤ የየቤቱ አጥርና ራዲዮ አፋልጉኝን ተያይዞታል፤ ወያኔም ለቆሪጥ ቢሾፍቱ ,,,,,,ጀመረ እንዴ!!!?) የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲጠብቁ የተሾሙት ፓትሪያርክ አላወገዙም። አልገሰፁም። ጳጳሳቱም ካህናቱም  አብረዉ ሁሉም ዝም አሉ። ግን ፀሐዩ ንጉሥ እየተባለ ይነገራል ይጸለያል።

ቅዱሱና የዋሑ ሕዝብ ፀሐይ ከጨለመበት ቆይቷል። ግፉ  ሲቀጥልም  ልዑል እግዚአብሔር እጁን መጀመሪያ ወደቤተመቅደሱ ዘረጋ በንጉሡ የተሾመዉን ፓትሪያርክ እርሱ ባወቀ  ,,,,,  እንዴት ብዬ ልናገር? ግን ዳግም ንጉሡ እጃቸዉን ወደቤተክህነት እንዳይዘረጉ ይማሩ ብሎ በሞት ቀጣ። ንጉሡ አልተማሩም። አሁንም የተስማማቸዉን መርጠዉ ሹሙ ብለዉ አቀረቡ። በድጋሚ እንደተለመደዉ ለፀሐዩ ንጉሥ ፓትሪያርክ ተሾመ። ለየዋሑና ቅዱሱ ሕዝብ አልተሾመም።
ጌታም ትዕግሥት ገንዘቡ ነዉና ዝም አለ። ይህ ሁሉ ሲሆን በተለይም በ60ዓ,ም አካባቢ ከታላላቅ ገዳማት ታላቅ መከራ እንደሚመጣ ለቤተመንግሥት በአባቶች በደብዳቤ መልዕክት ይላክ ነበር። ብዙ ባሕታዉያንና አባቶች የዛሬን አያድርገዉና ተደብድበዋል ታሥረዋል። ተገድለዋል። አይናቸዉንም አጥፍተዋቸዋል።

ይህ ሁሉ መከራ በሕዝቡ ላይ ሲደርስ በቤተመንግሥቱ ያሉ መሳፍንቱና መኳንንቱ ጳጳሳቱና ካህናቱ የጦር አለቆችና ወታደሩ በየገዳማቱ ያሉ አባቶች ሲጮኹ ዝም አሉ። ሕዝቡ በቤተመንግሥቱ በባንዳዎቹ በባለርስቶቹ በባላባቱና በጭቃ ሹም ያረሰዉን እህል ንብረቱን እየተቀማ ሲያለቅስ ዝም አሉ። የየገዳም አባቶች መልዕክት «መከራዉ በልጆቻችሁ ይደርሳል በልጆቻችሁ ይጀምራል» ያሉት ረብሻ በየትምህርት ቤቱ መሬት ላራሹ ተብሎ ተጀመረ። ቤተመንግሥቱ ፈጽሞ ልቡ ተደፍኗልና ከሚደርሰዉ ነገር ሁሉ ምንም ትምህርት መማር አልቻለም። በድጋሚ የተሾሙትም ፓትሪያርክ ለቤተመንግሥቱ ለመኳንንቱ የተሾሙ ስለሆነ ይህ ሁሉ ግፍ ሲደርስ ቤተእግዚአብሔር ሐዉልት ሲቆምበት ያለሥጋወደሙ ተክሊል እየተባለ ሲቀለድበት ሽፍንፍን እየተባለ ጾም ተሽሮ የቄስ ጾም የመነኩሴ ጾም እየተባለ ሰባቱ አፅዋማት ቀርቶ እየተመረጠ ሲጾም  መኳንንቱና መሳፍንቱ አራት አምስት ሚስት በየመሬታቸዉ ሲያስቀምጡ ሰንበት ሲሻር ደሀዉን ባለእርስቱ መኳንንቱ ሲጫወቱበት በገዛ ሀገሩ የሚርሰዉን ቦታ ሲያጣ በረሐ ለበረሐ ሲንከራተት የትናንት ልጆች መሬት ላራሹ ሲሉ  የንፁሐን ደም ሲፈስ ፓትሪያርኩም ለሕዝብ ስላልተሾሙ ከነጳጳሳቱ ከነካህናቱ ዝም። ሕዝቡም ስለቆሪጥ ያዉቃል፤ ዝም።እንግዲህ የጌታ ዝምታ ሁሉንም ነገር ሕዝብ እስኪረዳለት ድረስ ብቻ ነዉ። ጌታም ዝምታዉ አበቃ። አባቶች መከራዉ በልጆቻችሁ ይጀምራል እንዳሉት የካቲት 11-66ዓ,ም በመላዉ የኢትዮጵያ ት/ቤት ተዘጋ። የጌታ እጅ ወደቤተመንግሥቱ ተዘረጋ። 1/ ጌታ ቤተመንግሥቱን 2/ ንጉሡን 3/ መሳፍንቱንና መኳንንቱን 4/ ባለእርስትን ጭቃ ሹሙንና ባላባቱን 5/ በግፍ የሰበሰቡትን የጠንቋዩንና የባለዛሩን ሃብት ሁሉ መታ 6/ ፍርድ ያጓደሉበት ደሀዉ የበደሉበት ያስለቀሱበት የልዑልን  ቤተክርስቲያንን የደፈሩበት ሥልጣን ከዳቸዉ ዳግም ላይመለስ ንጉሣዊ ሥርዓት ተነቀለ ተደመሰሰ።

7/ የንጹሐንን ደም ያፈሰሱ የንጹሐንን ደም ያስፈሰሱ ዝም ያሉ ለቆሪጥ ሲገበር ንጹሐን ሕፃናት የትም ወድቀዉ እንደቀሩ ጌታ ባወቀ መሳፍንቱንና መኳንንቱ የፀሀዩ ንጉሥ ቅልቦች ባንድ ቀን የት እንደወደቁ ሳይታወቅ ባንድ ጉድጓድ ተጣሉ

8/ ንጉሡንም ሞቱ እንጂ እንስካሁንም የወደቁበትና የተቀበሩበት አይታወቅም (የወያኔ ዉሸት እንዳለ ይሁን)

9/ ከላይ የተባለዉ ሲፈጸም ዝም ያሉ የፀሀዩ ንጉሥ ፓትሪያርክም እንዲሁ ደማቸዉ ፈስሶ የት እንደወደቁ ሳይታወቅ ቀረ
10/ ሲያለቅስ ለኖረዉ መሬት ቢታደለዉም በቤተ መንግሥቱ የሚሠራዉን ግፍ ጠንቋይና ሟርተኛ ሲሾም ንጉሡ ለቆሪጥ ሲገብር እያወቀ ልጆቹን እየገበረ ዝም በማለቱ ጌታ በደርግ መላዉን ሕዝብ ልጆቹን ለወያኑ እንዲገብር አድርጎታል። ያ ዝምታ ነዉ እስካሁን ይኸዉ በመከራ የሚቀጠቅጠዉ። የአሁኑ ዝምታስ ምን ያመጣ ይሆን?

11/ ልዑል እግዚአብሔር የንጉሡን ዘሩን ሃብቱን ሠራዊቱን መታሰቢያዉን ሁሉ በተነ ካገር አጠፋ። ለመሆኑ ከዚህሁኔታ ቀጣዩ ፓትሪያርክ ምን ይማሩ ይሆን? ምንስ ይጠብቃቸዉ ይሆን?

ልዑል እግዚአብሔር በዚህ ቀጠለ። የዋሑ ወገናችን መሬት ላራሹ ተባለለት። ደሀ የተባለዉ ሁሉ ባለመሬት ተባለ። የዋሑ ወገናችን ባለእርስት ሆነ። ያረሰዉን ሰፈረ፤ አገባ። ጌታን አላመሰገነም። የጀመርከዉን አሳምርልን አላለም። ለጌታ ካረባዉ ከሰፈረዉ አሥራቱን አልሰጠም። ባለመሬት በመሆኑ ደስ አለዉ። ጨፈረ፤ ዘፈነ ሳተ ፋነነ ወገኑንም መበቀል ጀመረ።

በልዑል እግዚአብሔር ስም ሕዝባቸዉን ሲያታልሉበት በኖሩበት መሬት ላይ በልጆቻችን የተጀመረ ረብሻ ሄዶ ሄዶ የጠንቋይና የግፈኞች መነኻሪያ የነበረዉን ቤተመንግሥት ነቅሎ እግዚአብሔር የለም ብለዉ 120 ሆነዉ ራሳቸዉን «ደርግ» ብለዉ መሠረቱ። ልዑል እግዚአብሔር ሲካድ ጾም ጸሎት የአድሀሪዉ መሳሪያ ነዉ ተብሎ ሲሻር ማንም ወደልዑል እግዚአብሔር ስምህ ተካደ ብሎ ያለቀሰ ያዘነ የለም። ሁሉም ዘፈነ። ጊዜዉም ቀጠለ ወያኔም ሻዕቢያም የገዛ ወገኖቻችን በወገን ላይ ሥልጣን ፍለጋዉ ቀጠለ። የዋሑ ሕዝብም የቢሾፍቱ ቆሪጥ ግብር ሲነሳለት ልጆቹን ለሻዕቢያና ለወያኔ መገበር ጀመረ። ልጆቻችንን በግድ የእየተነጠቅን ለወያኔና ለሻዕቢያ ተገብረዉ እንደወጡ ቀሩ። ንጉሡ 40ዓመታት እንደገበሩ የዋሑ ሕዝብ ለሻዕቢያና ለወያኔ ለ17 ዓመታት ሲገብር ኖሮ አሁን ደግሞ ይኸዉ ለ23ዓመታት ከንጉሡ እንደተማሩት የስንት ንጹሐን ወገኖች መጥፋታቸዉ እንጂ የት እንደወደቁና እንደደረሱ አይታወቅም። ያም ሆነ ይህ አሁንም ኩሪፍቱና ቡሾፍቱ እየተባለ የቆሪጥ ነገር በየከተማዉ ሲወሳ ከሀገር ዉስጥ አልፎ ይኸዉ በስደት ዓለምም እየሰማነዉ ይገኛል። አሁንም ከጫካ ይጠጣዉ የነበረዉን የወገኑን ደም ከየዋሁ ሕዝብ መካከል ገብቶ አሁንም ወያኔ ይኸዉ እንደንጉሡ 23ኛዉን ዓመት ተያይዞታል። አቤት የጌታ ዝምታዉ? አቤት ትዕግሥቱ! ወያኔዎች ካለፈዉ ወይ ከደርጎቹ ወይ ክብጤያቸዉ ከንጉሡ አልተማሩ። እንኳ እንደንጉሡ ይህ 40ኛዉ ዓመት?! ---

ደርግ 17ዓመታት ጌታን ክዶ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ቀንም ሰላም አላገኘም። ቤተመንግሥቱ የሠራዉን ግፍ በደርግ ተበቀለዉ። ይህ ትምህርት ሊሰጠን ይገባል። ደርግ ቢመከሩ ሊመለሱ የሚችሉ ወጣቶችንና ስንት የሀገር ኩራት የነበሩ ምሑራንን ጨረሰ አስጨረሰ፤ ከሀገር አሳደደ፤ የተሰደደዉም ሕዝብ የነጭ ባሪያ ሆነ። የራሱን ትቶ እያኮረፈ እየወጣ የሰዉ ሀገር ይገነባል፤ ሌላዉ ጦርነት ዲቪ እየተባለ ምሑሩ እየተወሰደ ሀገሪቱ ምሑር አልባ ቀርታለች። ኢትዮጵያ ማን ይገነባሽ ይሆን? ሁሉም እየተሰደደ ነዉና።

ወያኔም ሲገባ ልጆቻችንን የጨረሰ ያስጨረሰ ጌታን የካደ መንግሥት ወደቀ ብለን ደስ ብሎን በእንባ ተቀበልን። ባለእርስት ያደረገንን ደርግን ዐይንህ ላፈር ብለን ረግመን አሳሰድን። ለጊዜዉ ልጆቻችን ከጦር ሜዳ የቀሩ ከሞት የተረፉ መሰለን፤ ደስ አለን። የተለመደዉ በጌታ ስም ማታለሉ ቀጠለ። ዴሞክራሲ ተባለ። ሰንበትበት ብሎ ደርግ በሕዝብ አስመርጦና እንደሐሳቡ አልሄድም ቢሉት በመርዝ ባስገደላቸዉ ቅዱስና የዋሑ ፓትሪያርክ ምትክ በንጉሡ የተለመደዉ እጅ በደርግ ቤተመንግሥትም እንዲሾሙ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የተሾሙት ፓትሪያርክ ላይ ስደት መጣ። በገሀድ ወያኔ ከምትጠፋ ከምትሞት ምረጥ ብሎ እንደሰማነዉ እንደንጉሡ ከቤተመንግሥት በቮልስ መኪና እንዳወጧቸዉ በቮልስ በፀሐይ እየነደዱ ኬንያ ጠረፍ ተጣሉ። ይህ በየጊዜዉ በቤተመንግሥቱ ትዕዛዝና ተፅዕኖ የሚሾሙት ፓትሪያርኮች ላይ የሚመጣዉ የልዑል ጌታ ቁጣ ፍፁም ትምህርት አልሆናቸዉም። አሁንም ጌታ በታላቅ ቁጣዉ መዓቱን ይቀጥላል የዚህች ሀገር የዋሕ ሕዝብ አምላክ አሁንም ዝም አይልም። ካለፈዉ አትማሩም ምን ዋጋ አለዉ?

ፓትሪያርኩ ጌታ መርጧቸዉ ቢሆን ኖሮ አደራ የተሾሙለትን መንጋ ጌታ እስከሞት ድረስ እንደወደደን ግደሉኝ ከሕዝቤ መካከል ልሙት አልሄድም ይቅርብኝ፤ ብሸሽም ሞት አይቀርም ተዋርጄ የሸሸ መንጋዉን

የበተነ ጳጳስ ተብዬ አልሞትም ባሉ ነበር። ጌታ ለበጎቹ ካልመረጠዉ ምንደኛ እረኛ ምን ይጠበቃል? ይባስ ብለዉ ከሀገር መዉጣታቸዉ ሳያሳፍራቸዉ አብረዉ ከተሰደዱ ስደተኛ ካህናትና መነኮሳት ጋ ሁነዉ እስከዛሬ ጌታ አንድ አድርጎ የጠበቃትን ሀገርና ቤተክርስቲያን ከወያኔና ሻዕቢያ መገነጣጠል ተምረዉ በሰዉ ሀገር ሲኖዶስ ብለዉ ያኮረፉና የወገን ተቆርቋሪ በመምሰል ቤተክርስቲያንንና ሕዝቡን ከፋፍለዉ ይቀልዳሉ። ከአንድ ሀገር ወጥተዉ ተቃዋሚ ፓርቲ እያሉ በሰዉ ሀገር እንኳን ሆነዉ የማይስማሙ አንድነት የሌላቸዉ ሕዝቦችንም ሰብስበዉ የሚተራመሱ አሉ። ቤተክርስቲያኗንም የፖለቲከኞች ምሽግ አድርገዉ ወንጌል እንሰብካለን (አምናለሁ ምንም ዓይነት የጌታ ወንጌል በእጃቸዉ እንደሌለ) ቀድሰን እናቆርባለን ይላሉ። ጌታችንና አምላካችን እርስበርሷ የምትለያይ መንግሥት ትጠፋለች ብሏል። ለመሆኑ ቤተክርስቲያኗን ለሁለት የከፈላችሁትም ሆናችሁ ተቃዋሚ ነን የምትሉ እንዲያዉ ምኞታችሁ ቢሳካና ፅዋዉ ሞልቶ በሌሎች ግፈኞች ላይ መዓቱን አዉርዶ ከሥልጣናቸዉ ገርስሶ ቤተመንግሥታቸዉን የደመሰሰ አምላክ ወያኔን ላያዳግም ቢጥለዉና ሀገር ብትገቡ፤ የማ ፓርቲነዉ ሥልጣን የሚይዘዉ? እስቲ ወደሀገር ቤት ሄድ እያላችሁ እየተጠበሰ ያለዉን ሕዝብ ለአፍታ ተመልከቱት። መሬት አለኝ ብሎ አይኮራ፣ ቤት አለኝ ብሎ አይኖርበት፤ አይሸጠዉ አይበደርበት፤ ባላሰበዉ ሰዓት እያፈረሱበት በየከተማዉ ዝናብ እየወረደበት ,,,,,,,የሚገኘዉን ወገናችሁን ሄድ በሉና ምን እንደሚል ስሙት። በመለያየት ፓርቲ እየመሠረቱ በነጩ ዓለም መደንፋት ለወያኔ ምኑም አይደል። ወያኔ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በፓርቲ ደህና አድርጎ በታትኖ ሥር ሰዶ እያሽቃነጠ ይገኛል። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ይባል ነበር።

ወያኔ ፓትሪያርኩን አሳዶ ባለስልጣናቱንና ምሑራኑን አባሮ ራሱ ፓትሪያርክ በቤተመንግሥቱ ትዕዛዝ እንደተለመደዉ ካለፈዉ ሳይማር፡-

1, የመጀመሪያዉ ፓትሪያርክ በጌታ ቁጣና መቅሰፍት ,,,, አይነገርም ዓረፉ፤

2, ሁለተኛዉም በጌታ ቅጣት ደማቸዉ ፈስሶ ዓረፉ

3, ሶስተኛዉ በመርዝ ተገደሉ ቅዱሱ

4, አራተኛዉ ተባርረዉ ተሰደዱ

5, አምስተኛዉ የወያኔ ፓትሪያርክ ,,,,,እንዴት,,,,,በቁም ነደዉ በበሽታ ተቃጥለዉ ,,,,,,አረ እንደዉ ይቅር,,,, ዓረፉ

6, ወያኔ ካለፈዉ አልተማረም ሁለቱንም በእጁ አስገብቷል፤ ቤተክህነቱም ቤተመንግሥትም የተመቻቸ ነዉ። አሁንም መርጦ የሾመዉን አስቀምጧል። ተሿሚዉም ያለፈዉን አላስተዋሉም ገቡበት። አይ ትዕግስቱ በዛ የጌታ! ፍጻሜያቸዉ እንዴት ይሆን?

## አስተዉሉ!!!

1 በልዑል እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ

2 ልዑል እግዚአብሔር በደሙ የመሠረታት አንድ ሁና የኖረች ቤተክርስቲያንን

3 በየዋሕነቱ አንድነቱን ጠብቆ የኖረ ቅዱስ ሕዝብ ከፋፍለዉና በታትነዉ መቅደሱን ቅርሱን እየዘረፉና እያቃጠሉ ቀልደዉበታልና እንግዲህ የፍርዱና የቁጣዉ ሰዓት አልቆ ተፈጻመ የወያኔዉን መንግሥት ራስ (ቁንጮ) እርሱ ጌታ ባወቀ መሪያቸዉን ፓትሪያርካቸዉን ባልጠበቁትና ባላሰቡት ሁኔታ በሞት ቀጣ፤ አሁንም አልተማሩም ዘረኝነቱም ልዩነቱም በሁሉም ቦታ እና አቅጣጫ ቀጥሏል። ጌታም እየደገሠ መሆኑን ይታወቃል።

## እነሆ ታላቅ ጩኸትና ጥሪ ለመላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በያለበት!

1 በመላዉ ዓለም ተሰድዳችሁ ያላችሁ ወዳችሁም ይሁን በግድ የወጣችሁ በእዉነት ኢትዮጵያዉያን ለሆናችሁት በሃይማኖት በዘርና በፓርቲ የተከፋፈላችሁ ሁሉ

2 በሀገር ቤት ያላችሁ ሁሉ በሃይማኖች በፓርቲ በዘር በብሔር የተለያያችሁ። በያላችሁበት በተለይም በየዋሑ ወገናችሁ ያስቡልናል በጎ ነገር ያደርጉልናል ብሎ ተስፋ የጣለባችሁ ምሑራንና እንዲሁም የሃይማኖች አባቶች ሁሉ

በየትም ቦታ ይሁን በሥልጣንም ላይ ያላችሁ በሠራዊቱም ያላችሁ ሁሉ አሁንም ሀገሪቱን በመምራት ላይ ያላችሁ፤ መቼም ወገኖቻችን ናችሁና ጥፋታችሁን አንሻም። አናንተም መከራችንን ጥፋታችን ደስ የማይላችሁ ትኖራላችሁና ይህን የ40 ዓመታት ሥቃይና መከራ ጨኸት የዚህን ቅዱስ የዋሕ ሕዝብ እንባ መፍትሔ የሚመጣበትን መንገድ እንሻለት (ለመሻት)

3 እስካሁን በሃይማኖትም ተከፋፍለን በዘር ተከፋፍለን በብሔር ተከፋፍለን በፓርቲ ተናጉደን ተሰዳደብን ተጋደልን ታሰርን ወያኔ ከቦታዉ ንቅንቅ አላለም። ጭራሹን ተቃዋሚዎች ወደሀገር ብትመጡ ,,,,, በምዕራብ ሱዳን መሬት ተሰጥቶታል ይወጋሃል

በሰሜን ኤርትራ ነዉ ዘመድ ነዉ እንዳይመስልህ ይወጋሃል።

በደቡብ ሱዳንና ኬንያ አያሳልፍህም ይወጋሃል፤

በምሥራቅ ሶማሌ አዲስ አበባን ይዟል ወዳጅ ነዉ ይወጋሃል። ከሀገር ዉስጥ ያለዉ ሕዝብ እንደምንሰማዉ ከተማዉ ሁሉ በጠቅላላ በፌደራል በሱዳንና በጋምቤላ ከጂንካ በታጠቁ ቋንቋ በማያዉቁ ወታደሮች ታጥሯል። ንቅንቅ ቢል እንደ97ቱ ግንባር ግንባሩን ይመቱታል። ታዲያ ለመሆኑ በሰዉ ሰዉኛ ወያኔ በቀላሉ በየባዕዱ ሀገር ሰልፍ እየወጡ መጮህ የሚጥለዉ ይመስልሃል? ወታደሩ እኮ በድሎት ተይዟል። ቤቱ እየፈረሰ ከሥራ እየተባረረ፤ ሱቁ እየተዘጋ፤ መሬቱ እየተነጠቀ ሁሉ ለወያኔ እየተሰጠ ሲሰቃይ እራሱን ለወያኔ የሸጠ ወታደር ፍርድ ሊሻ የሚያለቅሰዉን ወገኑን እየቀጠቀጠ የደረሰበት አይታወቅም። ስለዚህ የሚከተለዉን መፍትሔ ብዬ ያሰብኩትን በጋራ እንድንፈፅም ለመላዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ላዋይህ!!!

በሕያዉና በልዑል እግዚአብሔር ስም አምላችኋለሁ ፣ እለምናችኋለሁ እማልዳችኋለሁ! በኦርቶዶክስ እምነ ት ብቻ ያላችሁትን ደግሞ በቅድስተ ቅዱሳን በድንግል እመቤታችን ስም እለምናችኋለሁ!

1 በከፍተኛ ደረጃ የሰዉ ልጅ ሁሉ የተከገኘዉ የተወለደዉ ከአባታችን አዳምና ከእናታችን ከሔዋን በመሆኑ ዘረኞችና ብሔርተኞች ይህንን ከፉና እርኩስ የወያኔና የሂትለር ፍልስፍና ከሕሊናችሁ አዉጡና የአንድ አባትና እናት ልጆች መሆናችንን በማሰብ ራሳችሁን አንድ አድርጉ

(*እያሰቃዩን ያሉትም የገዛ ወገኖቻችን መሆናቸዉን አስቡ። ወጣም ወረደ ጥፋታቸዉን አንሻም ከእንግዲህ ኑሮ በጠበሰዉ ችግርና ወያኔ ባነደደዉ ሕዝባን ላይ ጦርነትን አንሻም።)

2 በሃይማኖትና በሲኖዶስ በየቤተክርስቲያኑ የተከፋፍላችሁ ሁሉ ልዩነቱን አዉጥታችሁ እኔና አብ አንድ ነን እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ,,, ብሎ እንደተናገረዉ ፈራጅ ቃሉ እንዳይፈርድብን አንድ ሁኑ

3 በሃይማኖት ስም ተከፋፍለን ቃሉን አፍርሰን ወንጌሉ እኮ እንዲት ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ይላል ያለፈዉ ዘመን ይብቃ ሕዝቡን የከፋፈልንበት በወንጌል ዙሪያ እንሰብካለን እያልን በቋንቋ በዘር በሃይማኖት እያለያየን አማራ ነፍጠኛ ጉራጌ ትግሬ እያልን ያሳለፍነዉ ጊዜ ይብቃና እራሳችን በማየት ያመቻቾንላቸዉ የግፈኞች ጊዜ አንዲ ያበቃ ከልብ አንድ አንሁን

4 ለወያኔ እድሜ ማራዘሚያ እስካሁንም ምቹ ሁኔታ የፈጠርንላቸዉ ባለሙያ እናቶቻችን እንደጦም ወጥ በየአይነቱ እንዲቀርብ ከተማሩ ምሑሮቻችን በያይነቱ የመሠረታችሁት ፓርቲ በየዕለቱ ግፍና ለቅሶ

ለበዛበት ወገን አንዳች አላደረገለትም እና ምሑራኑ ሁሉ እንግዲህ አንድ ሁኑ። ምናልባት ሀሳባችሁ ይህችን ቅድስት ሀገር ወያኔና ደርግ የቀለዱባትን ንጉሡ ዳንኪራ የረገጠባትን መኳንንቱ መሳፍንቱና ባንዳ የፏለለባትን አንድ አድርገን እንደቴዎድሮስ እንደዳዊት እንደዘርዓያዕቆብ እንደንግሥተ ሳባ እንደአጼ ካሌብ ሕዝቡንም ሀገሪቱንም ባንድነት ልትመሩ ከሆነ ተጠራሩና አንድ ሁኑና ተመካከሩ። መጀመሪያ ከስደተኛዉ(መቼም አያፍሩ) ሲኖዶስና ካህናት መነኮሳት ጀምሮ በግንባር ቀደምትነት አንድ ሁኑ ከዚያም

5 የነነዌ ንጉሥ መሳፍንቱና ሕዝቡ ሕፃናቱን ጡት ከልክለዉ እንስሳዉን ከበረቱ እንዳይወጣ አድርገዉ ጾም አወጁ (በሀገር ቤት ሲሰበክ እሰማ ነበር)

ለመሆኑ ከሀገር እየወጣችሁ ፓርቲ የመሠረታችሁ ሁሉ ከእንስሳቱ እናንሳለን እንዴ? የእንስሳዉንና የሕፃናቱን ጩኸት የሰማ ጌታ እኛን አይሰማንም?

## እንዲህ ይደረግ

ከሁሉ በፊት ሁሉም በየፊናዉ አንድ ይሁን ስደተኛዉ ሲኖዶስና በያለበት ያሉት አብያተ ክርስቲያናት አብረዉ ከሕዝቡ ጋር ይሰብሰቡና ኮሚቴ ይመረጥ

## የተመራጮች ተግባር

1 ከሕዝቡ ጋር ተነጋግሮ የጾምና የጸሎት ጊዜና ሰዓትን መወሰን (ያለማቋረጥ)

2 ሕዝቡ በአንድነት በጋራ ተገናኝቶ ምሕላ የሚያደርግበትን ቀንና ሰዓት ቦታ ደብር መወሰን፤ ቅዳሴም እንዲቀደስ ማድረግ

ማሳሰቢያ ሌሎች የእምነት ሰዎችም የራሳቸዉን ያድርጉ እኛ የማንንም ጥፋት አንሻም ወገንም አያልቅስ

3 ሕዝቡ ሕፃናቱንና ልጆቹን ይዞ ሳይሰለች በየቤቱና በየመሥሪያቤቱም ግፋችንን እያሰበ ወደልዑል እግዚአብሔር እንዲጮኽና እንደራሔል እንባዉን እንዲረጭ ማሳሰብ

4 እንደራሔል እንደሶስና (ግፍ) እንደአስቴር በመላዉ እስራኤል ሕዝብ ላይ የታወጀዉን ግድያ በዚያ አዋጁ በወጣበት ቤተመንግሥት ዉስጥ ሁና ጾም አዉጃ የተገኘዉን የጌታን ፍርድ ለሕዝቡ በተመሳሳይ እንዲያስተምሩ መምህራንን መጋበዝ

5 በግፍ እየተቃጠለ በእናት ሀገሩ ለሚኖረዉ ሕዝብ በየቤተክርስቲያናቱ ምሕላ አይፈቀድለትም ስለዚህ በየቤቱ ልጆቹን ይዞ እንዲያለቅስ ጥሪ ማድረግ

6 በሀገር ቤት ላሉት ታላላቅ ገዳማትጥሪዉን ማሠራጨት ጾም ጸሎትና ምህላዉን ማስቀጠል

7 ከተወሰነ ጾምና ጸሎት በኋላ በያለበት ካሉት ታላላቅ ምሑራን ጋር ጾታ ሳይለይ (የሃይማኖት ና የዘር ልዩነት ግባተመሬት ተፈጽሟልና) ከበድ ያለ ዉይይት ግፍ ስለሞላባት እናት ሀገራችሁ ማድረግ፤ ካስፈለገም ልዑል ጌታን በጸሎት ተጠይቋልና አንድ ወጥ ኮሚቴም በሉት ፓርቲ መመሥረት ይሆናል። ጌታ ያለበት ሁሉ ይጸናል። በወገን ላይ የሚደርሰዉን ግፍ በጸሎት ከሁሉ በፊት ለልዑል እግዚአብሔር ቀጥሎ በሀገር ዉስጥ ላለዉ ሕዝብና ወገን ለሆነዉ ሠራዊትና ተቆርቋሪ ለሆኑ ባለስልጣኖች ሁሉ ማሳወቅና ጸሎቱን መቀጠል

8 በሚደረገዉ ጾምና ጸሎት በተደረገዉ ፍቅርና አንድነት ዉስጥ ጌታ አንድ ቀን እንደአስቴር በሐማ ላይ የፈረደ ጌታ ዛሬም በዙፋኑ ነዉና ጌታ በዚህ ኮሚቴ ወይም የአንድነት ፓርቲ ለወገኑ በጾምና በጸሎት መልስ ይሰጣል። እሱ ጩኸታችንን ይሰማ ዘንድ የታመነ ጻድቅ ነዉና። እኛ በዚህ ሕዝብ ላይ ጦርነት ማወጅ አደለም ጌታ ለሕዝቡ የሚበጀዉን ያደርጋል። በእርሱ ላይ እንዉደቅ፤ መንገዱንም ይመራናል ጸሎተ ምህላ ላይ ቆይተናልና

9 ይህን ሃሳብ የደረሳችሁ ሁሉ ሳትንቁና ሳታቃልሉ ለሲኖዶሱ ለየአብያተክርስቲያናቱ ለካህናቱ ለየፓርቲዉ ሁሉ ተላልካችሁ ተወያዩና አንድ ሁኑ። ወያኔን ያለ ልዑል እግዚአብሔር፤ እንዲሁም ያለጾምና ጸሎት ሌላ ነገር ሊነቅለዉ አይችልም። በመለያየትና የፓርቲ ጋጋታ ሲያጠነክረዉና ሲያቆመዉ እንጂ ሌላ ነገር ሲያደርግበት አላየንም። እንግዲህ የምትሰሙኝ ከሆነ አንደ አስቴር በጾምና በሱባኤ በጸሎት ልዑል እግዚአብሔር ላይ መዉደቅ ይህ ጾምና ጸሎት ይነቅላቸዋል፤ የማንንም ጥፋት አያሳየን ልቡና ይስጣቸዉ።

ነጩ ዓለም የጦር መሣሪያ ያመርታል መሪዎቻቸዉ በጸጥታና በፍቅ ሁነዉ ለሕዝባቸዉ የሚያሻዉን አሟልተዉ እየበሉ እየጠጡ ዉስኪ እየተራጩ በመኪና እየፈነጩ በሰላምና በጸጥታ ብሔርተኝነት ዘረኝነትና ጦርነት ሳያሳስባቸዉ ይኖራሉ። ጀርመኖቹም ዳግም ላይገነባ የመለያየት ግንብ አፍርሰዋል። ይህንን ሁሉ የማይመለከቱ የአፍሪቃ መሪዎች ወርቁን ብሩን ከሀገራቸዉ ሕዝብ እየነጠቁ በገንዘቡ በገዙት የጦር መሳሪያ ጦርነት ከፍተዉበት በዘርና በጎሳ በሃይማኖት እየከፋፈሉ እያጋደሉ ገዳዮቻቸዉን ጀግና ብለዉ ወንድሙን የገደለዉን ይሸልሙታል። ነጮቹ በመሣሪያ በለወጡት ወርቅ ወገናቸዉንና ሀገራቸዉን ወርቅ አስመስለዉ በፀጥታና በሰላም ይኖራሉ። የአፍሪቃ መሪዎች የሀገር ሀብት እየዘረፉ በባዕድ ምድር እየደበቁ ወ,ናቸዉን የተማረዉን እያሳደዱ በንጹሃን ደም ግፍና ዕንባ እንደተጨማለቁ ለወገናቸዉ ሳይራሩለት አንድ ቀንም በሰላም ሳይወጡና ሳይገቡ ከነጮቹ ሳይማሩ በወገናቸዉ እንደጨከኑ ጨካኝ ታዞባቸዉ ሳያስቡት ለዘለዓለም ያንቀላፋሉ። ከሥልጣናቸዉም ይወድቃሉ፣ ይነቀላሉ።

የዚህ የጾምና ጸሎት ትልቁ ዓላማም ሥራዬ ብለዉ የተያያዙትን ግፍና ጭካኔ ከላያቸዉ ተነስቶ ወደልቡናቸዉ ተመልሰዉ በጽኑ ንስሀ ሁነዉ ይህንን በግፍ የሠሩትን ቤትና የሰበሰቡትን ገንዘብ መቼም አይጠቀሙበትም እባካችሁ በልዑል እግዚአብሔር ላይ እንዉደቅ። እልህ ጥላቻና ከንቱ ፉከራ ይብቃ! ወደሱ እንጩህ ኃይል የእሱ ብቻ ስለሆነ ይቻለዋልና አብረን እንለምነዉና ይገላግለን። እንደእራኤል ሕዝብ እንጩኸ እንደራሔልም እንባችንን ወደሰማይ እንርጨዉ እስከአሁን ያደርግነዉን ሁሉ እንርሳዉ ብቻችንን ነበርንና። አሁን ግን ልዑል እግዚአብሔርን ይዘን እንነሳ የምናደርገዉን ሁሉ ይመራናልና። አንድ ሁነን በብርቱ ወደሱ እንጩህ።
ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ አንድ ያድርገን በያላችሁበት ለምትገኙ እዉነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ሸክማችን የከበደ ግፋችንና ኃዘናችን የጸና የተጣልንና የተረሳን የወገኖቹ ጩኸት ይድረስ ለልዑል አምላካችን አሜን!

# በመጨረሻም

በሠለጠነዉ የነጩ ዓለም መሪዎች ሀገራቸዉን አልምተዉ ሕዝባቸዉን አስተምረዉና አበልጽገዉ እንደየደረጃዉና ዕድሜዉ ሥራ ፈጥረዉ ተተኪዉን ትዉልድ እንደሀገሪቱ ፍላጎት እያስተማሩ ከመለያየትና ከጦርነት ነፃ አድርገዉ ሕዝባቸዉን አምነዉ መሪዎቹም በሕዝባቸዉ ታምነዉ ሕዝቡ ኑሮዉና ሕይወቱ ተሻሽሎ ጸጥ ብሎ ለሀገሩ ዕድገት እየሠራ እየተማረና እየገነባ በደስታ እያደገ ይኖራል። የኛ (አፍሪቃ) መሪዎች ሥልጣን ሲይዙ ደም አፍስሰዉ ወገናቸዉን ገድለዉ የነበረዉን የልማት አዉታር አፈራርሰዉ የተጀመረዉን የትምህርትና የልማት መዋቅር አዉድመዉ የተማረዉን ኃይል ገድለዉና ከሀገር አሳድደዉ የራሳቸዉ ብጤ ያልተማረ ሰብስበዉ መንግሥት ይመሰርታሉ። በመሣሪያቸዉና በሥልጣናቸዉ ላይ ተቀምጠዉ የሀገራቸዉን ሀብት የሕዝቡን ርስትና ንብረት እየዘረፉ ለራሳቸዉ በባዕድ ሀገር በማስቀመጥ የሌላዉን ሀገር ባንክ ያደልባሉ። ባዕድ ይታዘባል አይሉም። ወገናቸዉን ሕዝባቸዉን በዘር በቋንቋ በብሔር በሃይማኖትና በፓርቲ በመሳሰሉት ይከፋፍሉታል። ሀገርና ሀብቷን እየሸጡ ሕዝቡን በረሃብና በችግር እየቀጡ ንብረቱን ንግዱን እየቀሙ ቤቱን እያፈራረሱ በመሣሪያቸዉና በሥልጣናቸዉ እያስፈራሩ እየቀጠቀጡ በወገናቸዉ ደምና እንባ እየታጠቡ መኖርን ተያይዘዉታል።

እነዚህን የሥልጣን ጥመኞችና ጨካኞች ያለ ልዑል እግዚአብሔር የሚገላግለን ኃይል የለምና በአንድነት እንሁን ይህንም የአንድነት ኃይል የሚመራ በጸሎት ተቋቁሞ በየስደት ሀገር ያለዉ ሁሉ በአንድ ስም በአንድ ማኅበር ሆኖ የመለያየት ሀሳብ ተቀብሮ በግፍ ሲቀጠቀጥ የኖረ የእስራኤል ሕዝብ በግብጽ በስደት እንዳለቀሰ አንድ ሁነንእናልቅስ በሀገር ላለዉም ሕዝብ ጥሪ ተደርጎለት በአንድነት ወደጌታ እንጩኸ።ወደፊት ስለሕዝባችንና ስለሀገራችን ነፃነት ምንም ነገር ቢተለም የአንድነት ፓርቲ ቢመሠረት አስፈላጊም ከሆነ ጦርነት ቢታሰብ እነዚህ የወገን ሀዘንና ለቅሶ የማይሰማቸዉ ግፈኞች ግፋችንን እናነሳም ቢሉ ስለሕዝባችንና

ወገናችን ለምንወስደዉ እርምጃ ልዑል አምላካችን በታላቅ ኃይሉና ክንዱ እንደሚረዳንና ብልሀቱን እንደሚያመለክተን እርሱ የታመነ አምላክ ነዉና። በዘር በጎሳ በቋንቋ በሃይማኖት በመሳሰሉት በመበታተኑ ለወያኔ ዕድሜ ማራዘሚያ ተመቻችቶ መከራዉን እየዛቀ ያለዉ ወገን ሁሉ መጀመሪያ ወደጦርነት ሳይሆን ያለምንም ቅሬታ በፍቅር በንጹሕ ልቡና አንድ ይሁን። ይህም የግፈኞችን መሠረት ያናጋልና ይታሰብበት። ሁሉም አንድሆኖ እንደሠለጠኑት አገሮች ስለሕዝባቸዉ ዕድገት ሰላምና ደስታ ነፃነትና ክብር እንደሚኖሩት መሪዎች ያሉ መሪዎችን አፍርተን ወገናችንን ከመከራ ለማሳረፍ የተበታተናችሁ ሁሉ ዳር እስከዳር መጀመሪያ አንድ ሁኑ። ተያይዘን እናልቅስ ምኞታችንና ዕቅዳችን ለልዑል ጌታ ይቅረብ።

አንድነት + ጸሎት + ኮሚቴ(ፓርቲ) + ዕቅድ + ሕግ + ትጥቅ + ትግል (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጦርነት) + ሰላም

## ይህ ሁሉ ሲደረግ ጾም፣ ጸሎት ፈጽሞ አይረሳም ሁሉም ወደልዑል እግዚአብሔር ይጮኽ ድል ለሚቀጠቀጠዉ ሕዝባችን ይሁን!

የወያኔ የወደፊት እጣ(ድግስ)

ሞትና መነቀል ይሁን ለወያኔ
አልቀር ቅንዳለቀስኩ ጌታ ካለጎኔ፤
እንባ ተቀባዩ አለልኝ መድህኔ
ለቅሶና ዋይታ ይሁን ለወያኔ
ታጭዶ አበቃና ክምሩ ተናደ
ደረሰና እንባችን እግዚአብሔር ፈረደ(ወረደ)
አስገመገመና ዝናቡ በረታ
ታጠቀ ወያኔ ለብርቱ ዋይታ (ዉካታ)
አልቅሰን አንብረተን ጠዋትና ማታ
ደረሰ እንባችን ለሀያሉ ጌታ
ተዘረጋ ክንዱ ወያኔ ተመታ
ተነስ ያገሬ ሰዉ በቃህ አታመንታ
ደስ ይበልሽ ነፍሴ ዘነበልሽ ደስታ
ታጠቂ ሀገሬ ለዘላለም ደስታ
ተነቅሎ ጠላትሽ ወደቀ ተመታ
ምስጋና ይድረሰዉ ለሠራዊት ጌታ
አሜን!!!

በ2007 መስከረም 3 በስደት መንደር ተጻፈች

ስደተኛዉ ወገናችሁ
ተስፋዬ አንተነህ፣ ጌታ ብቻ፣ ገብረመድህን፣ ቶሌቻ፣ ዋቸም፤

✝ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!✝